# የባዕድ ቅጥረኞች ሴራና የኢትዮጵያ ድርጅቶች

አምባቸው ሰዋስው

ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ ጠላቶች አሏት:: የትግራይ ገንጣይ ጠባብ ድርጅት አንዱ የውስጥ ጠላት ነው:: በአካባቢ ያሉ ፀረ ኢትዮጵያ ሀገሮች--እነ ግብፅን ጨምሮ-- ሌሎች ናቸው:: የሀገራችንን ዕድገትና ሰላም የማይፈልጉና የራሳቸውን ብሄራዊ ጥቅም ሲያሳድዱ ኢትዮጵያን የሚጎዱ የሩቅ ሀገሮችም መንግስታት አሉ:: ሁሉም ቅጥረኞች፤ ሰርጎገቦችና ሰላዮችን በስፋት ያሰማራሉ:: በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ድርጅቶች ላይ እየተካሄደ ያለውን የመከፋፈልና የማዳከም ሴራና ዘመቻ ስናይ ይህንን በቸልታ መያዙን ትተን በጋራና በቆራጥነት ነቅተን ልንታገል እንደሚገባ ሁላችንም መረዳት አለብን:: ይህ አጭር ፅሁፍ ተልዕኮው ይህን ማሳሰቢያ ለማስተላለፍ ነው::

በልዩ ልዩ ድረገፆችና መድረኮች በርካታ ሀገር ወዳዶች በሀቀኛ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ላይ የተከፈተውን ዘመቻ አጋልጠዋል:: በሚገባ ግልፅ ሆኖ ወይም ክብደት ተሰጥቶት ያልቀረበ እውነታ ካለ ግን ብዙዎቹ ፀረ ድርጅት ግለሰቦችና ስብስቦች በመለስ ዜናዊ ብቻ ሳይሆን በባዕዳንም ተገዝተው ዘመቻውን እያካሄዱ መሆናቸው ነው:: ይህን በማጋለጥ ስራ ድርጅቶቹም ራሳቸው ድክመት ማሳየታቸውም ሊጠቆም ይገባል:: ለሁሉም ግልፅ ሆኖ ያለው ጉዳይ በወያኔም ሆነ በባዕዳን እየተጠቁ ያሉት ሁለት ድርጅቶች ቅንጅትና ኢሕአፓ መሆናቸው ነው:: በእነዚህ ድርጅቶች የአመራር ቦታ ይዘውና ለወያኔም ለባዕድም አልበገር ያሉት የተከበሩ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልና ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት፤አቶ ኢያሱ ዓለማየሁና አቶ ፋሲካ በለጠ በስም እየተጠሩ በአምባገነንነት ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ደረጃም እየተወነጀሉና ስማቸው እየጠፋ ነው:: የወያኔው የሚታወቅ ነው:: በወያኔ መድረኮች፤ራዲዮኖች፤ድረገፆች አማካይነት የተከፈተው ፀያፍ ዘመቻ ያው የሚጠበቅ ነው:: ለባዕድ አድረው ለሀገር የሚያስቡ መስለው በኢትዮጵያ ልጆች ላይ ዘመቻ የሚያደርጉት ግን መጋለጥ ያለባቸው ናቸው:: ቅንጅትንም ኢሕአፓንም ለክፍፍል ሊያጋልጡ የተነሱት ቀንደኞች በሞላ ሳይሆን በከፊል ለባዕድ ማደራቸው እየተጋለጠ መሄድ አለበት:: ምንም እንኳን ሁሉ አንጃ የሲአይኤ ደሞዝተኛ ነው ባይባልም አንጃዎችንና ከፋፋዮችን ተመሳስለው የቅጥረኛ ስራቸውን የሚያካሂዱት ደግሞ ታውቀው መጋለጣቸው አስፈላጊ ነው::

የባዕድ ቅጥረኞች ልዩ ልዩ መለያና ሳይወዱ መታወቂያ አላቸው:: ከዚህ በፊት በዚሁ መድረክ ስለ ሰርጎገቦችና ሰላዮች ልዩ ልዩ ፅሁፎች መቅረባቸው ይታወሳል:: በቅንጅትና በመሪዎቹ ላይ ፀያፍ ዘመቻን በማካሄድ ግንባር ቀደም የሆነው ኤልያስ ክፍሌ ለምሳሌ ተብሎ የሚጠቀስ ነው:: ኢሳያስ አፈወርቂንና ዳውድ ኢብሳን እያደነቀና ለኢትዮጵያ የጠቀሙ እያለ ኢንጂነር ሀይሉን፤ ዶክተር ታዬንና አቶ አያሱን ከመለስ በፊትና በላይ ሀገርን የጎዱ ብሎ ለድምፅ ያቀረበው ይህ ግለሰብ ሲጀምር ልደቱ ከሀዲውን ደግፎ፤ከዚያም እነ ብርሃኑ ነጋን ኮንኖ ተገልብጦ ደግሞ የእነዚሁ የእነ ብርሀኑ ነጋ ደጋፊ በመሆን ቅንጅትንና የተከበሩ ኢንጂነር ሀይሉና ዶክተር ታዬን አብጠልጣይ ሆነ:: ኢሕአፓን የዚያድ ባሬና የሻዕቢያ ደጋፊ ብሎ እንዳላወገዘ ሁሉ አሁንም ዓይኑን በጨው አጥቦ የሶማሌ አክራሪዎችና የሻዕቢያ ደጋፊ ሆኗል:: በዚህ ሰልፉም ዛሬ የስዬ አብርሃ ዋና ተቃዋሚ ሆኖ ሲጮህ (ስዬ የእነ ብርሃኑና ፈቃደ ሸዋቀና አጋር ቢሆንም) በመሰረቱ የአንገቱ ላይ ቃጭል የሚሳበውና የሚደወለው ከወደ አስመራ መሆኑንም ጠቁሟል:: ይህ የአቅዋም መገለባበጥና በሕዝብ መሪዎች ላይ ፀያፍ ዘመቻ የታዘዘው በባዕዳን ለመሆኑ ደግሞ ብዙ መረጃን አይጠይቅም:: ወደ ኢሕአፓ ስንመጣ ይህ አንጋፋ ድርጅት ወደ አረጀ አንበሳነት መለወጡን የሚጠቁሙ ክስተቶች እንዳሉ ዛሬ ማወቅ ችለናል:: ሰርጎ ገብና ሰላይን በማገድ ለሌሎች ትምህርት ሊሰጥ የሚገባው ይህ ድርጅት ራሱን አጋልጦ አንድም እንኳን ሊመሩ ሲመሩም የማያውቁ አሳዛኝ ግለሰቦችን በአመራር ደረጃ ከማምጣቱ ሌላ ከዚህ ቀደም ድርጅቱን ሊበትን የተንቀሳቃሰና እኔ እኔ ባይ የባዕድ ሎሌን በድርጅት መልሶ ማስገባት ብቻ ሳይሆን በአመራርም መድቦ በራሱ ላይ ዳግም የብተናና የአንጃን መከራ አምጥቷል:: ይህ የቺካጎ ነዋሪና ዶክተር ዜሮ የሚል ቅፅል ስም የተሰጠው ግብዝ የግል ስልጣን ጥምና የሊቀመንበርነት ፍላጎት ያነሆለለውን አዛውንት ተጠቅሞ ኢሕአፓን ሊበትን መነሳቱ እነሆ እየታየ ነው::

እነዚህ የባዕድ ቅጥረኞች በምን ይመሳሰላሉ?

1. የድርጅቶችን ስም በማጥፋት
2. የመሪዎችን ስም በማጥፋት
3. የድርጅት ምስጢሮችን በማጋለጥ
4. የፈጠራ ሰነዶችን በማሰራጨት
5. በወያኔ ላይ ሳይሆን በታጋይ ድርጅቶች ላይ በመረባረብ

እስቲ በኤልያስ ክፍሌና በሌሎች በቅንጅትና ህጋዊ አመራሩ ላይ የተሰራጨውን የሀሰትና የፈጠራ ክስና አሉባልታ መለስ ብለን እናስብ። ክቡር ኢንጂነር ሀይሉና ዶክተር ታዬን በአፀያፊ ደረጃ ስማቸውን ለማጥፋት አልተሞከረም? የሀሰትና የፈጠራ ክሶች አልተስተጋቡም? ወደ ኢሕአፓ መለስ ስንል ደግሞ በዚህ አንጃ በተባለው በቺካጎው ዶክተር ዜሮ አማካይነት የ32 ገፅ ውስጣዊ ሰነድ በውጭ ያለነው ሁሉ እንዲደርሰን አልተደረገም? ይህ የአመራር አባል ነኝ የሚል ግለሰብ ስለ አመራር ስብሰባና ውሳኔ ከድርጅቱ ውጭ ላሉ ግለሰቦች ሳይቀር ያወራ አልነበረም? በቀይ ሽብር ወንጀለኞች በተሞላ ፓል ቶክ ተገኝቶስ በኢሕአፓ ሰማዕት ደም አልቀለደም? ነጋ ጠባ አምባገነን በሚላቸው መሪዎች ላይ በጣም ፀያፍ የሆነ የስም ማጥፋት ዘመቻ እያካሄደ አይደለም? በደፈናው እነዚህ ቅጥረኛ ግለሰቦች እንዳበደ ውሻ ሆነዋል ብሎ ማለፉ በቂ አይደለም:: ድርጅቶቹን ይጠላሉ:: አምርረውና ከወያኔ በበለጠ :: ኤልያስንም ሆነ ዶክተር የቺካጎ ዜሮን የሚያቃጥላቸው የቅንጅትና የኢሕአፓ መኖር መንቀሳቀስ ነው:: ዶክተር በሉኝ ባዩ የአፍራሽ ስራውን በይበልጥ ለመስራትና ለወያኔም ደፋ ደፋ ለማለት ሲል የኢሕአፓን ስም እስከ መንጠቅ ድረስ ሞክሯል:: በሰረቀው ራዲዮና ፓል ቶክ ብሎ በከፈተው መድረክ ሁሉ ዘመቻው በኢሕአፓ ላይ ነው:: ነገ ደግሞ ብዙ በሬ ወለደ ክስን ይዞ እንደሚመጣ የሚጠበቅ ነው:: እስከመቼ ነው የኢሕአፓ አመራር ይህን የኮሶ ትል በዝምታ የሚያልፈው?ለምን የሽሽት፤ የፍርሀት፤የብተና፤የካርቱም የአሜሪካ ኤምባሲ ግንኙነቱን፤ወዘተ ጉዱ አይጋለጥም? በቅንጅት ላይ የተከፈተው ዘመቻ በእነማን እንደሆነ ግልፅ ሆኗል:: በሀመርና ሊመዚን ተቀበልናቸው የተባሉት የይስሙላ ጀግኖች መጨረሻቸው ታይቷል:: የአውሮጳ ማህበርን አወናብደው በ1ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኦይሮ ድጋፍ ሊከፍቱት ያሰቡት ራዲዮም የሚሆንላቸው አለመሆኑን ማወቅ ተችሏል:: ኤንጂነር ሀይሉ በወያኔ ድጋፍ እየከበሩ ነው፤ እነ አቶ ኢያሱ አስመራ ሄደዋል፤ ወዘተ ወዘተ --የሚነዛው ሁሉ ታዲያ ምን ይጠበስ ቢባል ኩምሽሽ የሚል ነው:: ማን ቅጥረኛ ማን ለኢትዮጵያ ታጋይ መሆኑን ሕዝብ ያውቃል:: ማን ስዬ ጀግናችን ብሎ ለታጋዮች ገዳይ በራዲዮ እንደለፈፈና ማን ተገቢውን አቅዋም እንደያዘ ሕዝብ ያውቃል:: ማን ወያኔን እንደሚታገልና ማን ከወያኔ ጋር አብሮ ለመሰለፍና በጠረጴዛ ዙሪያ ተደራድሮ ለወያኔ ምርጫ አጃቢ ሊሆን እንዳቆበቆበ ሕዝብ ያውቃል::

በአንድ ድርሰት እንደቀረበው ጠና ያሉት ወይዘሮ አታላይ ግርማ ለተባለ ወጣት ውሽማቸው “አንተ ደግሞ ሳትተኛኝ አርግዢልኝ ” አትበል ያሉትን ያስታውሷል:: የፀረ ድርጅቶች ዓይነትና ይዘት ለየቅል ቢሆንም የእነ ኤልያስ፤ ፈቃደ ሸዋቀና፤የቺካጎ ዶክተር ዜሮ ዓይነቶቹ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: የሚያቃጭላቸው ሌላ ነው:: እንዳበደ ውሻ ድርጀቶቹንና መሪዎቹን የሚነክሱት አለምክንያት አይደለም:: የድርጀቶቹ መሪዎችን በተመለከተ የዝቅተኛነት ስሜት ስላላቸውም ጎትቶ ከትቢያ ለመጣል የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም:: የሕዝብን አመኔታ ያገኙትን ክቡር ኢንጂነር ሀይሉንና ሕዝብ ሁሉ ያደነቃቸውን ዶክተር ታዬን፤ ኢሕአፓን ከብተናና ከአንጃ ፃረሞት ከአባሎች ጋር ሆነው ያቆዩትን ፀረ ወያኔ መሪዎች እነ አቶ ኢያሱና አቶ ፋሲካን በሕዝብ ለማስጠላት የተከፈተው ዘመቻ ወያኔ ወያኔን፤ሲአይኤን ሲአይኤ መከርፋቱ የሚያስገርም አይደለም::  ይህንን መገንዘብ አቅቷቸው እነዚህን ፀረ ድርጅት ቅጥረኞች አምርረው የማይታገሉ ሁሉ በጥያቄ መግባታቸው ትክክል ነው:: ከኢዴኃጎ መሪዎቹ የተወሰኑት ከቅጥረኞቹ ጋር በፓል ቶክ መቅረባቸው አጠያያቂ ነው:: ኢሕአፓ የበኩሉን ውሳኔና እርምጃ መውሰድ አለበት:: ከዚህ ሌላ ደግሞ ሀገር ወዳድ ሀይሎች በሚገባ ተቀናጅተው የመጣባቸውን ጥቃት በጋራ መቋቋም አለባቸው:: ቅንጅት አንድ ነው--በታወቁ መሪው በኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የሚመራው:: ኢሕአፓ አንድ ነው--ልዩ ጉባዔውን ረግጦ ሳይወጣና ድርጅቱን ከወያኔ ጫማ ስር ሳይደፋ ራሱ ላይ ቅፅል ሳይጭን የሚታገለው:: ሌላው ሁሉ ወይ ተለጣፊ፤ወይ አንጃ፤ ወይ የባዕድ ቅጥረኛ ነው:: ለዚህም ነው ልናጋልጣቸውና ልንታገላቸው የሚገባው:: የሚመለከታቸው ንቀው ቢተዉትም እኛ ግለሰቦችና ኢትዮጵያን አፍቃሪዎች ግን

**ሰላይን ሰላይ ማለቱ አያቅተንም:: ሊገደንም ወይም ሊከብደንም አይገባም::ኤልያስም ዶክተር ዜሮም የሀገራችን ፀር የሆኑ ጌቶች አሏቸው:: ታዲያ ለምን ዝም ይባላሉ?**